# <u>በሀገር፣ በሕዝብና በቤተ ክርስቲያን ላይ በደል ሲፈጸም የጥንታዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቀሳውስት የሚያሰሙት ድምጽ</u>

August 4, 2014
11:00 EDT

Ethiopian Rally at Infront of State Department
Washington, DC

ቀሲስ ዶ/ር አማረ ካሳዬ እና ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ

*“ዘወሀብከነ ሥልጣነ በመንፈስ ንኪድ ኲሎ ኃይሎ ለጸላኢ ከመ ንፍታህ ዘኢይትፈታህ”* ማለትም፡- “ጠላት ሰይጣን እንዳይፈታ አርጎ የቋጠረውን የችግር ሰንሰለት እንፈታ ዘንድ የቅስናዋን መንፈሳዊት ሥልጣን የሰጠኸን አምላክ” እያልን በምንገልጻት ተልእኮ በጥንታዊት ኢትዮጵያ ኦርቶቶዶክ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ያሰማራንን አምላክ ስሙ የተመሰገነ ይሁን እያልን፤ እኛ ቀሲስ ዶ/ር አማረ ካሳዬ እና ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ሐምሌ ፳፰ ቀን ፳፻፮ ዓ/ ምህረት በዋሸንግተን ዲስ በተደረገው ሕዝባዊ ሰልፍ ላይ ይህችን የቤተ ክርስቲያን ድምጽ አቀረብን።

ከኛ በፊት በህዝባችንና በአገራችን ላይ መከራና ስቃይ በደረሰባቸው ጊዜዎች ሁሉ፤ አባቶቻችን ቀሳውስት የእምነትና የስነ ልቡና ምንጭ የሆኑትን ቃላት የተጻፉበትን (ታቦተ ሕግ) ተሸክመው በገጠር በከተማ በቆላ በደጋ በተራራ በሸለቆ አቀበቱን ቁልቁለቱን በመውጣትና በመውረድ ከህዝባቸው ጋራ የእምነታቸውን የዜግነታቸውንና የቅስናቸውን ሀላፊነት ተወጥተዋል። አሁንም ወያኔ/ኢህዴግ አሰባስቦ ባዋቀረው መንግስት ከህዝባቸው ጋራ ከደብራቸው የተሰደዱ የተገረፉ የተገደሉ፤ ቀሳውስት ብዙ ናቸው።

እንደሚታወቀው የተለያዩ የሰልፍ አይነቶች አሉ። ቤተ ክርስቲያን የምታወግዛቸው ጸረ ህዝብ ሰልፎች፤ ከስርአተ ጸሎታችን ጋራ የተያያዙ ሰልፎች እና ቤተ ክርስቲያን የምትከተላቸው ሕዝባውያን የሰልፍ አይነቶች አሉ። በማጭበርበሪያ መመሪያችሁ የውጭ ተመልካቹንም ኛንም እያታለላችሁ በህዝባችን ላይ የምትፈጽሙትን ግፍ አቁሙ ለማለት ሐምሌ ፳፰ ቀን ፳፻፮ ዓ/ ምህረት የተዘጋጀውን ይህን ህዝባዊ ትእይንት ቤተ ክርስቲያን የምትደግፈው መሆኑን ተረድተናል። በቅስናችን ግንዛቤ ይህ ሰልፍ ራሱንና አካባቢውን ይዞ እንዳይጠፋ የኢህዲግን መንግስት የሚያሳስብ፤ የሚያስጠነቅቅና የሚጠቅመው ደወል እንደሆነ እንገምታለን።

## <u>በእምነታችን የሚደርጉ ሰልፎች</u>

*“ስቡህ ወውዱስ ዘሳረረ ኲሎ ዓለመ”* ማለትም፡- “ዓለምንና በውስጧ ያለውን የፈጠረ አምላክ የተመሰገን ይሁን” ብለን የሁሉ ባለቤት የሆነውን አምላክ በማመስገን እንጀምርና *“ስምአኒ እግዚኦ ጸሎትየ ወይብጻህ ቅድሜከ ገአርየ”* ማለትም፤ “ጸሎቴን ስማኝ ጩኸቴም ካንተ ይድረስ” በማለት በእምነታችን ክበብ በፈጣሪና በተፈጥሮ ፊት እንሰለፋለን።

*“ተንስኡ ለጸሎት”* በማለት ህዝቡን እየቀሰቀሰን “ሰላም ለኩልክሙ” በሚለው ቃል የምንፈጸመው ቅዳሴ ሰውነትን በተወሀደው መለኮት ፊት የምናደርገው ሰልፍ ነው። ሕገ ኦሪትን ጥሰው በህገ አራዊት [ሙሉ ሀሳቡን ለማግኘት ይህን ሰንሰለት ይጫኑ:-] ተሰልፈው የሚመጡትን ወራሪዎች ሕገ ወንጌልን መከተል ቢከብዳችሁም ቅሉ፤ አትግደሉ፤ ድንበር አትጣሱ፤ ከሕገ አራዊት ወደ ሕገ ኦሪት ተመለሱ፤ የሚለውን መልእክት ለማስተላለፍ፤ ጽድቅ ሁሉ በተፈጸመባት በጥምቀት በዓልና፤ ጻድቃን ሰማእታት ለእውነት የተሰውባቸውን ገድላት ለማሳሰብ በቅስናችን ታቦተ ሕጉን ተሸከመን የምናደርጋቸው ዑደቶች ሰልፎች ናቸው። ወገን በሞት ተለይቶን ወደ መቃብር የምንሸኝበትም የጉዞ ፍታት ሰልፍ ነው። ባቀራረባቸውና በይዘታቸው ይለዋወጡ እንጅ፤ በሰላም፤ በደስታ፤ በሀዘንና በልቅሶ ሀሳባችንን ስሜታችንን የምንገልጽባቸው ቅኔዎቻችን፤ ውዳሴዎቻችና ዜማዎቻችን ሁሉ ሰልፎች ናቸው።

አውደ ምህረቶች የህዝብ ድምጽ ማፈኛዎች፤ እንዲያውም የዓመጽ መልእክት ማሰራጫዎች ሲሆኑ፤ ደጀ ሰላሞች የሰላም የመረጋጋት መከታተሚያዎች መሆናቸው ቀርቶ፤ የትርምስ የሽብር ደጆች ሲሆኑ፤ ቀሳውስት ከላይ የተገለጹትን በእምነታችን ዙሪያ የሚደረጉትን የሰልፍ አይነቶች ይዘው ከሚጎርፈው ህዝባዊ ሰልፍ ጋራ እንደ ገባር ወንዞች በመቀላቀል ወደ አደባባይ ይወጣሉ። ኢትዮጵያዊት ቅስናችን የማትሳተፋቸው ይልቁንም የምታወግዛቸው ጸረ ሰብ ሰልፎችም አሉ።

## <u>የኢትዮጵያ ኦ.ተ. ቤተ ክርስቲያን ቅስና የምታወግዛቸው ጸረ ህዝብ ሰልፎች</u>

ሙሶሊኒ በኢትዮጵያ ላይ ወራሪ ጦሩን ሲልክብን፤ በሮም ከተማ ላይ ሴቱን ወንዱን ሁሉ ያሰለፈብን ጸረ ህዝብ ሰልፍ ነው። ይህ አይነት ሰልፍ ጸረ ሰብ እንጅ ሰላማዊ አይባልም። በታሪካችን ጎልቶ የሚነገረውን ለምሳሌ ያህል ጠቀስን እንጅ፤ ይህን የመሳሰሉ

ጸረ ሰብ ሰልፎች በዓለም ላይ ተፈጽመዋል። ይህ አይነት ሰልፍ ተወራሪውን ህዝብ ዳር ድንበሩን አዛንፎ፤ ዜግነቱን ሰርዞ፤ ክብሩን ገፎ፤ ሰውነቱን አዋርዶ፤ በቋንቋ በጎሳ በድንበር ከፋፍሎ፤ ኃይሉን አዳክሞ፤ እርስ በርስ አናክሶ፤ እርስ በርስ እያጋደለ ለመኖር የተዘጋጀ ሰልፍ ስለሆነ ቅስናችን የምታወግዘው ሰልፍ ነው።

እንደነ ሙሶሊኒ ያሉ ወራሪዎች፤ ላቀዱት ወረራ ከህዝባቸው ድጋፍ ለማግኘት በኢትዮጵያ ላይ የሚያዘምቱትን ሠራዊት ለመሸኘት ካሰለፉት ወረራ እጅግ የከፋ፤ ቅስናችን የምታወግዘው ጸረ ህዝብ ሰልፍም በዘመናችን በሀገራችን ተከስቷል። <u>ይህም ሰልፍ፤ ለከፋፋይና ለአናካሽ ፖሊሲው ደጋፊ ያለው አስመስሎ የኢህዲግ መንግሥት ለውጭ ተመልካች ለማቅረብ፤ እየቀጠቀጠ የሚገዛውን ህዝብ አስገድዶ ያሰለፈው ሰልፍ ነው።</u> ይህ አይነት ሰልፍ ሄዋንን በራሷ ላይ እንድትዘምት ያስደረገ፤ በፈታኝ ወጥመድ የገባ ህዝብ፤ ራሱን በራሱ እንዲያጠፋ በፈታኙ ወራሪ ተገዶ የሚሳተፈው ሰልፍ፤ ከወራሪዎች ሰልፍ የከፋ ኢትዮጵያዊት ቅስና ያረፈችበትን ንጹሕ ህሊና የማያስተኛ ጸረ ሰብ ሰልፍ ነው።

አገር ለማፍረስ፤ ህዝብ ለማፍለስ ፤ ታሪክ ለማቃወስ አስቦና አቅዶ የገባ ወያኔ ያዋቀረውን ኢህድግን መሳይ መንግስት ይቅርና፤ በዘውዳዊ ውርስም ሆነ፤ በህዝብ ምርጫ በተሰየሙ መንግሥታት ላይ ተቃዋሚ አለባቸው። እጅግ የሚያሰጓቸውን ሰዎች ካንድ ክልል እንዳይወጡ በክብር ያግዟቸው ነበር። ከክልሉ ወጥቶ በሰው አገር ተሰዶ የሚኖረውን ግን፤ የሰው አገር ድንበር እየጣሱ የሚገድሉ መንግሥታት መኖራቸውን እስከ ኢህዲግ መንግስት ዘመን ድረስ አልሰማንም።

ይህ በዘመናችን የተከሰተው በወያኔ የተዋቀረው የአቶ ኃይለ ማርያም መንግሥት ግን፤ ተቃዋሚውን ቢችል የሰው አገር ጥሶ በመግባት መግደል፤ ያን ማድረግ ባይችል አፍኖ ወስዶ በማሰቃየት ይተባበረው ዘንድ ያስጠጋውን መንግስት ከእኩይ ተግባሩ ጋራ ማሰለፉን ቅስናችን የማትቀበለው ነው።

## <u>የኢትዮጵያ ኦ.ተ. ቤተ ክርስቲያን ቅስና የምትቀላቀለውና የምትስማማበት ሰልፍ</u>

ወቀሳን ፍርድን እየጨመሩ ዓመጽን በራሳቸው ላይ የሚከማቹ፤ በህዝብ ላይ የራስ ምታትና የልብ ድካም የሚያተርፉ፤ መላ ሰውነትን የሚያቆስሉ፤ ምድርን ባዶ የሚያደርጉ፤ ለም ቦታዎችን ለባእዳን አሳልፎ ለመስጠት የሚሰለፉ ሰዎች የሚከሰቱ ጉዶች እንዳሉ ነቢዩ ኢሳይያስ *"ደግሞስ ዓመጻ እየጨመራችሁ ለምን ገና ትቀሰፋላችሁ? ራስ ሁሉ ለህማም ልብም ሁሉ ለድካም ሆኗል። ከእግር ጫማ አንስቶ እስከ ራስ ጤና የለውም። ቁስልና እበጥ የሚመግልም ነው። ምድራችሁ ባድማ ናት። ከተሞች በእሳት ተቃጠሉ። እርሻዎቻችሁንም አይናችሁ እያየ ባእዶች ይበሉታል (ኢሳ 1፡6__8)* እያለ ተናግሮ ነበር።

ነቢዩ ኢሳይያስ የገለጻቸውን ጸረ ሕዝብ ባህርያት ሳያዛንፍ በሥራ ላይ ያዋለ መንግስት አለ ከተባለ፤ ዓመጽና ግፍ እየጨመረ በሀሰት በሸፍጥ የህዝቡን ራስ እያዞረ ፤ ከራሱ እስከ ጥፍሩ ድረስ፤ ማለትም፤ ከጅምሩ እስካሁን ድረስ የሚናገረውና የሚያደርገው የህዝብ ህሊና እያቆሰለ፤ ገዳማትን መንደሮችን ባድማ እያደረገ፤ የእርሻ መሬቶችን ከህዝብ እየነጠቀ ለባእድ አሳልፎ የሰጠ፤ በዘመናችን ኢትዮጵያ ላይ የተከሰተው እውነትን ያንቀጠቀጠ ኢህዲግ መንግሥት ብቻ ነው።

<u>ቤተ ክርስቲያናችን ዓለምን በህዝቧ፤ ህዝቧን በዓለም ውስጥ ለመረዳት ለሚያስችሉት biblical, historical, cultural, lithrgical theology ለሚባሉት ሙያወች ተጠያቂ የሆኑትን ሊቃውንት እየደመሰሰ፤ በምትካቸው አገርንና ህዝብን ለመከላከልና ለመታደግ የሚደረገውን ይህን መሳይ ሰልፍ፤ ፖለቲካ ነው በማለት ህዝቡን የሚያፌዙ ተራ ሰዎችን እየሰበሰበ ዓላማውን ማስተጋባት በሚያስችሉ አጫጭር ኮርሶች፤ ቀሳውስት፤ ቆሞሳት፤ ጳጳሳት ሰባኪዎች እያደረገ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የሰገሰገ መንግሥት ነው።</u>

የራሱን የተቀደሰ ጋብቻ አፍርሶ፤ ለሰው ትዳር መፍረስም ጠንቅ ሆነብን ለተባለው ሁሉ አስመሳይ ቄስ፤ መነኩሴና ቆሞስ ገብቶ መቀደስና ማቁረብ የሚችል መሆኑን የሚሰብኩ፤ ለሞራል ለእምነትና ለይሉኝታ ጠበቃ ሆና የቆየችውን የቀሳውስት ውግዘት በበራሪ ወረቀት አንስተናል በማለት ህዝቡን የሚያሰናክሉ፤ ቤተ መቅደስ የግል ንብረትና መተዳደሪያ እንዲሆን የሚደግፉ፤ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ባይታወር የሆኑ ጳጳሳትን ያሰማራ መንግስት ነው። ለሞራልና ለስነ ልቡና መለኪያ ሆና በኖረችው በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ <u>ሀሰት፤ ሸፍጥ፤ ማታለል፤ ማስመሰልና ዝሙት እንዲስፋፉ ይህ መንግስት በሚሰጠው ድጋፍ ላይ ትዝብታችን ተርፎና ተትረፍርፎ አጠለቅልቆናል። ኢህዲግ ፓትርያርክ አርጎ የሰየማቸው አቡነ ማትያስ በበቂ ማስረጃ ህዝብ ያቀረበላቸውን የታደሰን</u> [*ሙሉ ሀሳቡን ለማግኘት ይህን ሰንሰለት ይጫኑ፡- <u>በቀድሞው ቄስ ታደሰ ሲሳይ ላይ በምእመናን እና በሶስት ቀሳውስት የተላለፈ ቃለ ውግዘት</u>*] <u>ተደራራቢ ስህተት እንደማያውቁና እንዳልሰሙ አፍነው መያዛቸው በቂ ማስረጃ ነው። ምንም ግዝቤ ለሌለው አዲስ ተክል</u> [*ሙሉ ሀሳቡን ለማግኘት ይህን ሰንሰለት ይጫኑ፡- <u>አባ ፋኑኤል አዲስ ተክል ናቸው</u>*] <u>ለተባለው ግለሰሰብ አሳልፈው መስጠታቸው</u> በጠቅላላ ኢትዮጵያና በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የተከሰቱት ሁሉ አስነዋሪ ተግባራት የዚህ መንግስት አመራር ትሩፋቶች ናቸው። የዚህ ሁሉ ጥርቅምና ድምር ውጤት ይህን ሰልፍ እንድንቀላቀለው አስገድዶናል።

በኢህዲግ ዙሪያ የተሰበሰቡ ጉዶች፤ አደጋ ያደርሳሉ ተብለው ለሚገመቱት ቡድኖች ዓለም የሰጠውን የአሸባሪነትን ቅጽል፤ ከስህተታችሁ ታረሙ እያሉ በሚቃወሟቸው ንጹሀን ዜጎች ላይ እየለጠፉ ለተመልካች ያቀርባሉ። በሌላ በኩል ደግሞ፤ ከባህላችን ውጭ ሆነው የሚያስቸግሩትን የሕጻናትን ጠባይ የምናርምበትን ታራሚ የምንለውን ቅጽል በስነ ምግባር ከነሱ ይልቅ እጅግ

በላቁት ዜጎች ላይ ለጥፈው ማቅረባቸውም፤ አቶ አስራት አብርሃም በጻፉት መጻፉቸው ላይ ሲገልጹ "እውነቶችን ያንቀጠቀጡ ጉዶች" ብለው ያቀረቡባቸውን ምስክርነት ከሚገባ በላይ አረጋግጦልናል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከላይ የተገለጹትን ተደራራቢ በደሎችን የሚፈጽሙትን ለመክሰስ፤ ለመውቀስ፤ ለመገሰጽ፤ ለመከላከልና ለማስቆም የሚደረግ ሰልፍ፤ ፈጣሪና ተፈጥሮ የሚቀበሉት ሰልፍ ነው። ይህን ዓይነት ሰልፍ ቤተ ክርስቲያን ትመራለች። ይህን አይነት ሰልፍ የሚመሩትንም ትቀላቀላለች። ያም ቢያዳግት ትከተላለች። ይህን የመሰለውን ሰልፍ ከመምራት፤ ከመቀላቀልና ከመከተል መገለል ግን፤ ከፈጣሪና ከተፈጥሮ ራስን መቁረጥ ነው። የራስን ህልውና እንደልነበረ ማድረግ እና፤ ይህን የመሳሰሉትን ሰልፎች በመምራት ረዥሙን ዘመናት ያቋረጠችውን የኢትዮጵያን የቅስና ታሪክ መካድ ነው።

<u>በዚህ አፍራሽ መንግስት ወጥመድ ተይዘው ሲናገሩ ካየናቸው ከአቶ አንዳርጋቸው ንግግር በስተጀርባ የሰማነው የስቃይ ዘግናኝ ጩኸት፤ አስነዋሪ ተግባራችሁን አቁሙ በማለቱ ከሚገረፍ ወገናችን አካል ሰንጥቆ ከኝ የደረሰ የስቃይ ድምጽ ነው። የኛም አካል በግርፋቱ ወላፈን እየተጠበስን ነው። ኢህድጎች አውቀውም ሆነ ሳያውቁ አቶ አንዳርጋቸውን አሳዝለው ያቀረቡልን ይህ የወገን የጩኸት ድምጽ፤ ሁላችንንም እንቅልፍ ነስቶናል። ይህን ሰልፍም እንድንሳተፍም አስገድዶናል። ይህን የጩኸት ድምጽ ሰምተው ከዚህ አይነት ሰልፍ እራሳቸውን ያገለሉ ቄሶች፤ "ዘመድ ቄስ እየፈታ ያለቅስ" ብሎ ባህላችን ከሚገልጻቸው ቀሳውስት ውጭ ሆነው ራሳቸውን ባእድ ያደረጉ ናቸውና፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ከሚገልጸው ቅስና እራሳቸውን በራሳቸው ያገለሉ ናቸው።</u>

የዛሬዋ ሰልፍ "ወደፈተና አታግባን" *[ሙሉ ሀሳቡን ለማግኘት ይህን ሰንሰለት ይጫኑ:- <u>"ወደፈተና ኢታግባን"</u>]* ከምትለው ጋራ አባቶቻችን "ከወዳጅ ጠላት አድነን" የሚሏትንም ባህላዊት ንግግር የምናስታውስባት ሰልፍ ናት። ዛሬ በወገንና በአገራችን ላይ የሚፈጸመው ግፍና መከራ፤ ወራሪ ጠላት በሚወረው ላይ ከሚፈጽመው ግፍና መከራ ጋራ ቢመሳሰልም፤ ይህን ሁሉ መከራና ግፍ በህዝባችን በመፈጸም ላይ ያሉት ከውጭ የመጡ አይደሉም። ነቢዩ ኢሳይያስ "ልጆች ወለድኩ አሳደኩ። እነሱ ግን አመጹብኝ" (ኢሳ 1፡2) እንዳለው፤ ኢትዮጵያ ወልዳ ያሰደገቻቸው ናቸው። እነዚህን ጉዶች ኢትዮጵያዊት ቅስናችንም <u>በጡት ነካሽነት</u> ትከሳቸዋለች።

ይህን የሰላም ሰልፍ የጎረጥ እያዩ አያገባንም በማለት ያልተካፈሉ ሁሉ ቄሶች፤ ነቢዩ ኤርምያስ በሰቆቃው ምሬቱ፤ "ከትንሹ እስከ ትልቁ ለግል ጥቅም የሚስገበገቡ፤ ነብያቱ ካህናቱ ሳይቀሩ የሚያጭበረብሩ፤ የህዝቡን ቁስል እንደ ቀላል የቆጠሩ፤ መፍትሄ ለመፈለግ የማያስቡ፤ የህዝቡን ቁስል ማየትም የማይፈልጉ፤ እንዲያውም ሰላም ሳይኖር፤ ሰላም የሚሉ፤ ስለ ጸያፍ ስራቸው እፍረት የሌላቸው፤ ስለዚህ ከሚወድቀው ጋራ የሚወድቁ ናቸው (ኤር ፮፡፲፫—፲፭)። ብሎ በገለጸው ተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ወድቀዋል። ከዚህ አይነት ሰልፍ ራስን መደበቅ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን ቀሳውስት ባህርይ አይደለም። በህዝቡ ላይ የወደቀው መከራ ሲከብድና ዘመኑ ሲረዝም፤ "አስጨናቂዎቹ ራስ ሆኑ ጠላቶቿም ተከናወነላቸው" (ሰቆ 1፡5) እያለ እንደጮኸው እንደ ነቢዩ ኤርምያስ ቀሳውስት ልንጮህ ይገባናል። እንደ ኤርምያስ ያሉ፤ ኤርምያስን የሚመስሉ ሁሉ ቀሳውስት የሰላም እንቅልፍ ሊኖረን አይገባም።

አገር ለተወለዱባት ሁሉ እናት ናት። ከጥንታዊት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን የተቀበልናት ቅስናችን በመንፈስ ለተወለድንባት ለዘላለማዊቷ ህይወት እውነትን የምንመሰክርባት፤ መንፈሳዊት ትምህርትን ሰንቀን፤ ህዝቡንም በዚህ ስንቅ እንዲሳተፍ የምናደርግበት ናት። ከዚህም በተጨማሪ ጎልቶ የሚታየውን ይህን መሳይ የተደራረበ ስህተት በግልጽ የምንገስጽባት ናት። ከአመጽ ብዛት የተነሳ የቅስናችን ተግሳጽ ተቀባይነት ሲያጣ፤ ተፈጥሮ ይተባበራት ዘንድ "ሰማይ ስሚ ምድርም አድምጭ" (ኢሳ 1፡2) እያለች ምስክርነቷን ለፈጣሪ ለማቅረብ፤ ከወንድማችን ከአንዳርጋቸው ንግግር በስተ ጀርባ ከሰማናት የስቃይ ድምጽ ጋራ ትተባበራለች። <u>የተገፋው ህዝብ ተገዶና አማራጭ አጥቶ የራሱን ጦርነት ጀምሮ ንጹህ ደም ከመፍሰሱ በፊት፤ የተፈጥሮ ይግባኝ ሰሚ የሆነው አምላክ፤ አቶ መለሰንንና አቡነ ጳውሎስን በራሱ መለኮታዊ ጦርነት እንዳስወገዳቸው፤ አሁን ያሉትንም ግፈኞች እኛ በመናውቀው ረቂቅ ጥበቡ አስወግዶ፤ ነገሮችን ሁሉ አሁን ላለውና ለመጭው ትውልድ በሚጠቅም መንገድ ያከናውናል ብላ ኢትዮጵያዊት ቅስናችን ታምናለች።</u>

ህጻናት እየቦረቁ ፤ ጥጆች እየፈነጩ ባካባቢያቸው እንዳያድጉ፤ ጎልማሶች ትዳር ንብረት እያፈሩ አባቶቻቸውን በመተካት በቅያቸው እንዳይኖሩ። የቤት እመቤቶች ጸንሰው፤፤ ወልደው አሳድገው ፤ ድረውና ኩለው እንዳይኖሩ፤ አዕሩግና እቤራት ለልጅልጆቻቸው ባህላቸውን፤ ለዛቸውንና ታሪካቸውን እያወረሱ ንስሀ ገብተው ቆርበውና ሰግደው ቀሪ ዘመናቸውን በሰላምና በቡራኬ እንዳይፈጽሙ የሚደረገውን ግፍና መከራ ቢቻል "ከመ ንፍታህ ዘኢይትፈታህ፤ ወአረቀ ማእከሌነ" በምትለው ክህነታዊ ግዴታችን በሰላምና በእርቅ ለማስቆም፤ ባይቻል ግን የሚቆምበትን መንገድ በመሻት ከተሰለፉት ወገኖቻችን ጋራ የመሰለፍ ግዴታ አለብን። ይህንን ከባድ ሃላፊነት በእግዚአብሄር ረድኤት ወደተግባር ለመለወጥ በገለልተኝነት ቆማችሁ ለምትመለከቱ በተለይም በውጭ ላላችሁ ቀሳውስት ወገኖቻችን ትተባበሩት ዘንድ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የሁላችንንም ድምጽ እግዚአብሔር ተቀብሎ የመከራውን ዘመን እስኪያሳጥርልን ድረስ "አቤቱ ወደ አንተ መልሰን እኛም እንመለሳለን። ዘመናችንን እንደቀድሞው አድስ" እያልን ከሚጮኸው ህዝባችን ጋራ ጩኸታችንን እንቀጥላለን።